የእናት ፍቅር

ክፍል - 2

.....ይቅርታ ልጄ እንድትናደጂብኝ አልፈልግም ግን ያው ላንቺ ብዬ እኮ ነው ::ስትል ግን በሎ ነገር የለም በቃ አልኳት አንገቷን አቀረቀረች አይኖቿ እንባ አዘሉ እንዳትጎጂብኝ ስለምፈልግ እኮ ነው ልጄ አለች አንገቷ እንዳቀረቀረች እረ ..... አልኳት እንደማፌዝ ብዬ.....

አዋ ልጄ ስለሱ በቻልሽው መጠን ለማወቅሞክሪአለችኝበጣምተናደድኩባትበቃምንአይነትመንፈስእንደያዘኝአላው ቅምእናቴይህንታክልፈትየነሰኳትምንበድላኝነውእላለውአንዳንዴበቃለራሴ የማላውቀው ነገር ሆኖብኛል አንድ ቀን ሰፈር አከባቢ ከፍቅረኛዬ ጋር እያለሁ እናቴ ከገብያ እየመጣች ነበር በጣም ብዙ ዕቃ ይዛላች እኔ እና እሱ ተቀምጠን

ነበረ አያትና ምን አለበት ከምትሸም ከፍላ ለሰራተኛ ብታሸክም ምንአይነኋ ቋጣሪ ናት ብሎኝ እንርዳት እንዴ አለኝ በርግጥ እሱ እናቴ እንደሆነች አያውቅም አሌክስ ባክህ አርፈህ ተቀመጥ አልኩት እንዳታየኝ ብዬ ፊቴን አዙሬ ተቀመጥኩ እሷም አይታኝ እንዳላየ አይታኝ ባላዬ አለፈችኝ ግን ውስጤ ትንሽ ቅር አለው እንዴት የፈለገ ቢመጣ ሰው በእናቱ ያፍራል አልኩኝ በዚህ መሀል ቁጭ ብለን እያለን ሜሪ ምንላት ጓደኛዬ መጣች

ሲበዛ ቅንጦት ትወዳለች እናቷ ጋር በውሀ ቀጠነ ነው የሚጣሉት አንዴ ቤታቸው ሂጄ እሷ ከ እናቷ ጋር ሲጨቃጨቁ ሳይ እናቷ በጣም ነበር ያስጠላችኝ ጥፋቱ ግን የሜሪ ነበር እናቷ ልብሷን ሳይቀርምየምታጥብላት

+251-920-59-46-52 @achirlebwold አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
E-Mail: stefantekka52@gmail.com Fax 251-11-11-11 Addis Ababa, Ethiopia

የእናት ፍቅር@achirlebwold

እናቷናት እንደዚህም ሆኖ ግን እናቷን ታማራለች ትልቅዬው ወንድሟ ደግሞ ከሰፋ ይብሳል በቃ ላያቸው ሰው እናታቸው ናት ለማለት ይከብደዋል አይደለም ለእናት ይሄን ታክል ጥላቻ ይቅርና የማያውቁትን እንኳን እንደዚህ መጥላት አይቻልም ሜሪ ሰላም ብላን ቁጭ አለች ደብሯታል አሌክስ በመሀል አጠገቤ ተቀምጦ ሚሴጅ ላከለኝ ሳየው እሱ ነው ። እንዴ ምን ሆኖ ነው አብረን ሆነን ሚሴጅ የሚልክልኝ ብዬ የላከልኝና መልክት ከፍቼ ሳነበው ሜሪ እኮ አርግዛለች እኮ አለኝ በጣም ነበር የደነገጥኩት ምክንያቱም ከዚህ በፊትም እንደዚሁ አርግዛ አቦርሽን አድርጋለች በጣም ተናደድኩ ድጋሚ እንደዚህ አይነት ጥፋት ውስጥ መግባቷ ምንሁነሽ ነው አልኳት ምንም እሷም አለችኝ ነው ብዬ ተነስቼ ወደ ቤትሄድኩ እናቴ ራሷን አሟት ተኝታለች ስታየኝ መጣሽ የኔልጅ እኔ የምልሽ ሊዲያ እኮ መጣለችጠየቅሻት አለችኝ ሊዲያ ማለት በጣም የምወዳት ጓደኛዬ ነበረች ከስድት አመት በፊት ነበር ለስራ ወደ አረብ ሀገር የሄደችው ሊዱ ለእኗቷ ያላት ፍቅር ላየ ሰው ግራ ነው የሚገባው ማነው እናት ሊዲያ ናት ወይስ እናቷ ናት እናት ይባላል ። ለእናቷ ስትል የማታደርገው ነገር የላትም ሰፈራችን ነበሩ እሷ ወደ አረብ ከሄደች በኋላ ቤትሰርታላት ሰፈር ቀይረዋል መምጣቷን ዛሬ ሰማሁ ግን አልሄድኩም አሁን ልሄድ ነው አልኳት ውስጥ ገብቼ ልብሴን ለባብሼ ወደውጭ እንደወጣሁ አልክስንና ሜሪን ሳይ በቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ.....

#ይቀጥላል...

☎ +251-991192111 @stefantekka
+251-920-59-46-52 ✉ @achirlebwold አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
E-Mail: stefantekka52@gmail.com Fax 251-11-11-11 Addis Ababa, Ethiopia